# ማን ያውራ የነበረ ቁ. 12

አንዳንድ ታጋይ ነን ባይ ድርጅቶች ፍቅሬ ክላሽ ብለው ሲዘፍኑ የተሰማ ቢሆንም ትግል ሰርግ፣ ድግስ ወይም ፈንጠዝያ አይደለም፡፡ የአንድ ሕዝብ፣የአንድ ሀገር የወደፊት ዕጣ፣የነገ መልክ፣ ነፃነት ወይ ባርነቱ የሚወሰንበት ሊሆን የሚችል ነውና በቀላሉ ከቶ ሊታየ አይገባውም፡፡ ስለዚህም ትግል ብለው ለቁንጥና ለጧልት፣ለይስሙላና ለማወናበድ ያልተነሱት ሁሉ ማለትም ትግልን በሚገባ የተረዱ ሁሉ በቅድሚያ የትግላቸውን ይዘትና አቅጣጫ ይወስናሉ፡፡ ይህንንመ የሚያደርጉት የሀገራቸውንና የዓለም አቀፉን ተጨባጭ ሁኔታ በተገቢው መንገድ መርምረው ማነው ጠላት ማነው ወዳጅ የሚለውን ለይተው አውቀውና የትግሉንም ስልት በሚገባ ተረድተው ነው፡፡ በተገቢው አነጋገር እናስቀምጠው ከተባለ የህብረተሰቡንና የዓለም አቀፉን ዋና ዋና ቅራኔዎች ዘርዝረው ቀዳሚውን ከተከታዩ፣ዋነኛውን ከመለስተኛው፣ሊታረቅ የሚችለውን ሊታረቅ ሊጣጣም ከማይችለው ለይተው ያስቀምጣሉ ማለት ነው፡፡ ኢሕአፓ ቅራኔዎችን አያያዝ በተመለከተ ባሳለፈው ተመክሮ የተሳሳተባቸው ወቅቶች ቢኖሩም በመሰረቱ ግን የህብረተሰቡን ቅራኔዎች ቀደም ተከተልና ይዘት በሚገባ ተረድቶ፣ቅራኔዎችንም ቢገባ ይዞ ትግሉም ሊያጧጡፍ ሞክሯል፡፡

ኢሕአፓ ትግል ሲጀምር በሀገሪቷ የነበረው ዋና ቅራኔ የአፄውን ሥርዓት ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያቃረነው በመሆኑ ድርጅቱ ሰፊውን ሕዝብ በአንድ ጎራ አሰልፎ በገዥው መደብ ላይ ለማሰለፍ ፕሮግራም ተልሞ ተንቀሳቅሷል፡፡ ይህን በሚያደርግበት ወቅትም በብሄረሰብ ልዩነትና ጭቆና ደረጃ የተከሰተውን ቅራኔ ይዘት በመረዳትም መብትን በማክበርና በጋራ በመታገል ችግሩን ማስወገድ ይቻላል የሚል አቋሙን አስተጋብቷል፡፡ በዚህም የተነሳ የብሄረሰብ ቅራኔ የማይታረቅና በመገንጠል ብቻ ሊፈታ የሚችል ነው ብሎ ፥ፕሮግራም ካሰራጨው የወያኔ ድርጅት ጋር ቅራኔ ገባ፡፡ ይህም ቢሆን የተከሰተውን ልዩነት በውይይትና በሰላም እንፈታለን በሚል እምነት በወያኔ ላይ በጦር ሳይዘምት ቆይቶ ከትግራይ ካልወጣችሁ ባይ ለነበረው ወያኔ ጊዜን ስጠው፡፡ወያኔም በዚያ ሳይወሰን፥ በወንዝ ማዶ አጋሮቹ ተደግፎ በኢሕአፓ ሠራዊት ላይ ጦርነት አወጀ ፡፡ በዚሁ ወቅትም ሆነ ቀደም ብሎ ድርጅቱ ከልዩ ልዩ ኃይሎች ጋር ለማበርና ተግባብቶ ተቻችሎ ለመስራት እየጣረ ነበር፡፡ለወያኔም ቢሆን ያቀረበው አማራጭ በፓርቲ ደረጃ በርዕዮትና ፕሮግራም ከተስማማን ውህደት፣ አሊያም የጋራ ግንባር፣ይህ ካልሆነ ደግሞ ዝቅ ባለ ትብብር ተወስኖ መቻቻል የሚል እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል፡፡ ዛሬ ታሪክን ነጋ ጠባ ማጅራት የሚመቱ ኢሕአፓ እኔ ብቻ እንጂ ሌላው ድርጅት ይጥፋ ባይ ነበር ብለው ቢቀጥፉም ድርጅቱ አቋሙ ይህ እንዳልነበር ሀቅ ነው፡፡ የደርግ የህብረት ጥሪ በተሰራጨም ጊዜ ኢሕአፓ የሰጠው መልስ ሁሉን ድርጅቶች /ወያኔንም ጭምር/ ና የሲቪክ ማህበራትን ያቀፈ ሂደት መሆን አለበት የሚል ነበር፡፡ ኢሕአፓ በጎንና ለብቻው ከደርግ ተደራድሮ ጥቅማ ጥቅም ሊያሳድድና ሌሎችን ድርጅቶች ሊጎዳ በፍፁም አልጣረም፡፡ እንግባባ አሊያም አንቻቻል ብሎ ሁሉን ድርጅቶች ቀረበ እንጂ ጉልበት አለኝ ባለበት ድርጅቶችን ሊወጋ አልተነሳም፡፡ ከመኢሶንም ጋር ቢሆን በአዲስ አበባ የምስጢር ውይይቶችን አካሂዶ ነበር፡፡ ኢሕአፓ በፕሮግራሙም በሰላም ለመታገል ፍላጎቱን አስፍሮ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ደርግና አጋሮቹ ጦርነት አውጀው እስኪዘምቱበት ድረስ ቅራኔ/ን አባብሶ ጥይት መተኮስ ላይ አልተሰማራም ነበር፡፡ ይህ ሌላ ሊደበቅ የማይችል ሀቅ ነው፡፡

ቅራኔን በሚገባ ለመያዝ ቅራኔዎችን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ወዳጅና ጥላትን ያልለየ ትግል በሽክላ ድስት መሰብር ደንብሮ ገደልእንደገባ በሬ ይሆናል፡፡ ወዳጁን ይመታል፣ጠላቱን ያቅፋል፣ ትግሉን በአፍጢም ይደፋል፡፡ ወያኔ የብሄረሰቦች ቅራኔ ዋና ነው ሲል ሕዝብን እርስ በርስ በማጋጨትና አማራ በሚለው ሕዝብ ላይ ደግሞ ጥላቻን በመፍጠር ትግልንም ሀገርንም ጎድቷል፡፡ በየካቲት አብዮት ጊዜ ኢሕአፓና መኢሶን ሊለያዩ የበቁት ጠላት ማነው በሚለው ላይ ነው፡፡ኢሕአፓ የምርጥ መኮንኖቹ አገዛዝ የሕዝብ ጠላት ነው፣ወርዶ በሕዝባዊ ጊዜያዊ መንግሥት መተካት አለበት ሲል መኢሶንና ሌሎች ደግሞ ይህ አገዛዝ በሂስ እየተወቀሰ ሊደገፍ የሚገባው ነው ብለው ነበር፡፡ ወደ ወያኔ ስንመለስ፥ ሕዝብንም ሀገርንም ጠላት ብለው ፈርጀው ያካሄዱት ትግል ለባዕድ ጠላቶች ሳይቀር በር ከፍቶና መዘዝ አስከትሎ እነሆ ሀገሪቷን ሊያወድም እየተፈታተነ እያለ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በወያኔ ወይም ዛሬ ይበልጥ ጠቦና ከስሞ የመለስ ቡድን በሚባለውና በኢትዮጵያ ሕዝብ መሀል ያለውን መሠረታዊና ዋና ቅራኔ ዛሬ መካድ

ወይም አላይም ማለት ከቶ አይቻልም:: በሁሉም መስክ ከሕዝብ ተፃርሮ፤በዝባዥና ጨቋኝ ሆኖ፤ ለሀገር ህለውና አደጋ ሆኖ፤ የሕዝብ መብት አፋኝ ሆኖ ያለው ይህ የመለስ አገዛዝ ነው:: ኢትዮጵያ አንድነቷና ህልውናዋ ተጠብቆ፤ሕዝቧ የዴሞክራሲና የመብት ባለቤት ሆኖ እንዳይገኝ አንቅፋት የሆነው ይህ የመለስ አገዛዝ ነው:: ስለዚህም ከዚህ አገዛዝ ጋር ሕዝብ ያለው ቅራኔ ዋና በመሆኑ ሕዝብ በአንድ በኩል አገዛዙ  ጭፍሮቹ በሌላ በኩል ሆነው÷ ለሞት ሽረት ትግል ተፋጠው ይገኛሉ:: ይህን መሠረታዊ ሀቅ መገንዘብ አቅቷቸው፤ተስኗቸው ወይም ያ መከረኛ ሆድ ጋርዷቸው አገዛዙ ወዳጅ ነው የሚሉ ካሉ የቅራኔ አፈረጃጀትን ሀ ሁ መማር የሚኖርባቸው ይሆናሉ:: አገዛዙ ከነጭፍሮቹ በተቃራኒው ጎራ ሲመደቡ÷ ሌላው ሕዝብ በሞላ ግን በወዳጅ ደረጃ የሚፈረጅ ነውና በመሀሉ ያሉትን ወያኔዎችን በመለስተኛ ደረጃ ይዞ በአግባብና በሰላም ለመፍታት መጣር ያሻል ማለት ነው::አንዳንድ ድርጅቶች ግን ለራሳቸው ተቃዋሚ የሚለውን ስም ቢሰጡም የመለስን አገዛዝ በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ከመሆኑ በላይ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ያላቸውን ልዩነት በተመለከተም እያካሄዱ ያሉት ዘመቻ መለስተኛውን ቅራኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚወስድ ነው:: ይህ ልዩነትን በሚገባ መያዝ አለመቻል÷ በህብረት ጥረቱ ላይ ያስከተለውን መዘዝም ያየነው ነው:: አለወቅቱና አላግባብም ወደ ታሪክ መለስ ብለው የፈረደበትን ኢሕአፓን ነጋ ጠባ በመወንጀልና የአፀያፊ ዘመቻቸውም ኢላማ በማድረግ የሚንቀሳቀሱትም እየፈፀሙ ያሉትይህንኑ ስህተት ነው::

ኢሕአፓ በውስጡ የተከሰቱ ችግሮችንም ከሞላ ጎደል በአግባብ በመያዙ ዛሬ ከአገዛዙ ጎን ቆመው ሊከሱት የሚጥሩትንም ቢሆን ተቀዋማችሁ ብሎ ሳይገደላቸው በሰላም ያሰናበታቸው ናቸው:: ኢሕአፓ መታገል ያልፈለገንና በቃኝ ያለን አባሉን እንደ ወያኔ እያሰረ የሚገድል ድርጅት ሳይሆን የሚያሰናብት እንደነበርም ይታወቃል:: በአንድ ወቅት ለቀውት በሌላ ወቀት ተመልሰው የሚቀላቀሉትም ጥቂት እንዳልሆኑም የታየ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢሕአፓ በዋናው ፀረ ሕዝብ ኃይል ላይ በማተኮር ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያለፉትንና ወይም መለስተኛ የሆኑ ቅራኔዎችን በመተው የጋራ ትግልን ጠቃሚነት በማስቀደም ህብረት ብሎ  ሲጥር ዓመታት አልፈዋል:: ኢዴኃቅ አንድ ምሳሌ ነው:: ከዚያም ለጥቆ ለግዮኑ ጉባዔ ለበቃው ሂደት ዋና ተሳታፊ ነበር:: ኢዴኃኅን ለመመስረት በተደረገው ጥረትም ጉልህ ሚና ነበረው:: የሌሎች ድርጅቶች ደጋፊዎች ነን ወይም ሁሉን አዋቂ ረዳትም÷ ሙሉ ፕሮፌሰሮች ነን ያሉት ሁሉ ሲረባረቡበት፤ በቀድሞው አገዛዝ ሽብርና ወንጀል ተሳትፈው ያፈሰሱት ደም እየኮረኮር የሚያጮኻቸው ሁሉ በራዲዮና በየጋዜጣቸው ቢዘምቱበትም÷ ከህብረቱ አልራቀም:: ሌሎች ድርጅቶች ያረቀቁትንና  ያመኑበትን የትግል ሰነድና ፕሮግራም እንዲሁም ስልት ተቀብሎ፤ማን ትልቅ ማን ትንሽ ሳይል በእኩል ከሌሎች ጋር ህበረት መሰረተ እንጂ አልሸሸም:: ከህብረቱ የወጡና በድርጊታቸውም ለመለስ ቡድን የጠቀሙ እነማን እንደሆኑ ሕዝብ ጠንቅቆ የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: ነጋ ጠባ ግን ለእንቅፋቱም፤ለንግድ ኪሳራውም፤ ለገጠመኙ ሁሉ ኢሕአፓ ላይ ማላከኩ የሚያዋጣ አልሆነም/አልነበረም:: ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮም ቢሆን ኢሕአፓ ሲበዛበት ይካላከላል እንጂ÷ በተዘመተበት ቁጥር አፀፋውን ልስጥ ብሎ አይደክምም:: በዚህ በኩል ይንቃል ቢባል ክሱን ይቀበላል::

የሕዝብ ጠላት የሆነን ኃይል እንደ ወዳጅ ስለቆጠርነው ብቻ ጠባዩ አይቀየርም:: የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ይውረድ-ይውደም ለምን አላችሁ የሚሉን ክፍሎች እነሱ በተላሰለሱ ቁጥር አገዛዙ መቆርፈዱን የሚቀንስ እየመሰላቸው ነው:: ይህ ደግሞ ስህተትና ሊሆንም የማይችል ነው:: የቅራኔን ይዘት ማወቁ ለትግልም አቅጣጫና ይዘት ወሳኝ ነው:: ለወዳጅ እንጂ ለጠላት ሎሚ አይያዝም:: መንግስቱ ኃይለማርያም ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ ይባል የነበረው÷ የሚያሳየው አምባገነኑ ወዳጆቹን ማወቅ ተስኖት ግራ ቀኙን አጥፍቶ ለውድቀቱ ራሱም ድልዳል እንደሰራ ነው:: ኢሳይያስ አፈወርቂም ወዳጅና ጠላትን መለየት አቅቶት ነው ከዋና ሎሌው ከመለስ ዜናዊ ጋር ሊጣላ የበቃው:: ይህ የገዢዎች ስህተት ለትግላችን ጥሩ መሆኑ ባይካድም ዋናው ትኩረታችን በራሳችን አካሄድና የትግል ፈር በመሆኑ ዋናውን ቅራኔ ከመለስተኛው እንዳናማታ መጠንቀቅ ወሳኝ ነው:: በብሄረሰቦች መሀል ያለውን ሁኔታ የመለስ ቡድን እያረገበ ሕዝብን ለመከፋፋልና በመጨረሻም ሀገሪቷን ለመበታተን እየጣረ ነው:: የሀገሪቷን አንድነትና የሕዝቧን አብሮ መኖር የሚመኙ ክፍሎች ይህንን የአገዛዙ  ርጉም ስምሪት ሊያጅቡ አይጠበቅባቸውም:: የኦሮሞ ሕዝብ መብት ተቆርቋሪ ነን ብለው የሚታታሙ አንዳንድ ጋዜጦች ሆኑ÷ የተደራጁ ክፍሎች ያላቸው አቋም አገዛዙ  የሚረደና ሕዝብን የሚያቃርን መሆኑን ከዚህ በፊትም የጠቀስነው ነው:: የኦሮሞ ሆነ የሌሎች መብት ተነፈግን የሚል ሕዝብ ጠላት አገዛዙ እንጂ ሌላው ሕዝብ አይደለም:: በሕዝበ ላይ ከሚደርሰው በደልና ጭቆና ተጠቅሞ የበለፀገ የአማራ

ሕዝብ አልነበረም፡፡ዛሬም ከመለስ ቡድን ዘረፋና ግፍ የትግራይ ሰፊ ሕዝብ ተጠቃሚ ተደርጎ ተወስዶ በጣለትነት ሊፈረጅ አይችልም፡፡ ይህን መሳት ለእነ መለስ መጥቀምና የሕዝብን ትግል በከፍተኛ ደረጃ መጉዳት ነው፡፡ የጭቆናው መወገድ ዴሞክራሲን መስፈን ግድ ይላል እንጂ በሆነ ሕዝብ ላይ በጅምላ በጥላቻ መዝመትን አይጠይቅምም፡፡

ቅራኔ በሁሉም ህብረተ ሰብ የሚከሰትና ለዕድገትም አስፈላጊ የሆነ ነው፡፡ ቅራኔ በመከሰቱ መደናገጥ አይገባም፡፡ ድርህቶች መሀል ፉክክርና ቅራኔ መኖሩም የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህ ቅራኔ በሚገባ ሳይያዝ ቀርቶ አቅጣጫ ከሳተ፥ ወይም ሚዛኑ ከከበድ ያኔ በርግጥም ስህተት ተፈፅሟል ማለት እንችላለን፡፡ ኢሕአፓ የሌሎች ድርጅቶችን መኖር አይቃወምም፡፡ በህገራችን ድርጅቶች በሁለት ሶስት ይወሰኑ የሚል አጓጉል ፀረ ዴሞክራሲ አቋምም ሲያስተጋባ አይሰማም፡፡ ድርጅቶች ኖረው በሕዝብ ድጋፍ ይፋፋሉ፤በድጋፍ ማጣት እንጂ  ጫጭተው ይጠፋሉ ብሎ ያምናል፡፡ ለአቋሙ እንደሚከራከረው ሁሉ ሌሎችም ለፕሮግራማቸው መቆማቸውን በፀጋ የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ፕሮግራሜ ይሻላል ብሎ ማለት ደግሞ መብቱና የሚጠበቅ ነው፡፡ ከራሱ ፕሮግራም ባሻገር ደግሞ ለጋራ ትግል ሲል በጋራ ለተቀበለው የትግል ፕሮግራም ይቆማል፡፡ ሌሎችም ባመኑበት የመሰለፍ የመቆም መብታቸውንም ያከብራል፡፡ መደረግ ያለበትን የህሳብ ፍጭት ሆነ ትግል ሲያካሂድም እንደ ቆሰለ አውሬ ሁሉን ለመንከስ በመነሳት ሳይሆን ፥ በስነ ስርዓት ነው፡፡ የሕዝብ ትግል ይጎዳል ባለበት ጉዳቱ ከየት እንደሚመጣ ማስረዳትና ሕዝብን ጠንቀቅ እንበል ማለት ግዴታው ነው፡፡ ተግባሩን የተከታታሉ  ሁሉ ሊረዱ እንደሚችሉት፥ በቀይ ሽብር ዘመን ወንጀል የፈፀሙበትን ሳይቀር በቁርሾ ዛሬ ካለተፋረድኩ ብሎ ሳያወግዝ ለዛሬው ፀረ ወያኔ ትግል ህብረት እንቅፋት ሊሆን የሚችለውን ሁሉ በማስቀደም ጋሬጣዎችን አልዘረጋም፡፡ እነዚሁ ክፍሎች ግን የሌባ ዓይነ ደረቅ ሆነው ተመልሰው ኢሕአፓን ሊከስሱ ሊወነጅሉ ሲነሱና ሲያበዙትም ማሳሰቢያ ሰጥቷቸዋል፡፡ ትኩረታችንን ከዋናው ዒላማ ወደ ሌላ ማዞር የአገዛዙ ፍላጎትና የሰርጎ ገቦቹ ሥራ ሲሆን፥ ይህንን ባለመረዳት ሆነ ይሁነኝ ብለው ፍሬ ቢስ ንትርክና ግጭትን የሚያራግቡ ክፍሎች በተጨባጭ የአገዛዙ ጀሌዎች ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡

በህገራችን ዛሬ ዋናው ቅራኔ ሕዝብን እርስ በርሱ የሚያጋጨው አይደለም፡፡ በደርጅቶች መሀል ያለው ቅራኔ አይደለም፡፡ በልዩ ልዩ ርዕዮተ ዓለሞች መሀል ያለ ቅራኔ አይደለም፡፡ የህብረተሰባችን ችግሮች ሁሉ እንዲፈቱ ከተፈለገ ዋናው መፈታት ያለበት ቅራኔ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለው ቅራኔ ነው፡፡ ይህ ቅራኔ ካልተፈታ ሌሎች ቅራኔዎች ሊፈቱ አይችሉም፡፡ ለምሳሌ ሕዝበን ከባዕድ ጠላቶች ጋር የሚያቃርነው አለ ፡፡ ይህንን ለመፍታት ወይም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር በቅድሚያ ሉዐላዊነቷን የሚያስደፍረውን አገዛዝ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ብሄረሰቦች የመበት ያለህ ይላሉ፡፡ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና እኩልነት እንዲረጋገጥ ጨቋኙና ጠባቡ አገዛዝ መወገድ አለበት፡፡ወዘተ ወዘተ!! በመጀመሪያ መቀመጫዬን አለች ዘንጀሮ እንደተባለው በመጀመሪያ የሥልጣኑን ጥያቄ መመለስና ሥልጣንን ወደ ሕዝብ እጅ መመለስ ያሻል፡፡ ይህ ደግሞ በአገዛዙ በጎ ፈቃድ የሚሆን አይደለም፡፡ ለአፄው ለርካታ ዓመታት አቤቱታ ቀርቦ፥ ምክርም ተለግሶ ነበር--ተገቢውን ምክር የሰጣቸው አብዮት ነው፡፡ ዕብሪተኛው መንግስቱ ጠያትነት ከጃጅሎት ስለነበር፥ በሰው የሚመከር ባለመሆኑ ያው በሕዝብ ትግል ውርደቱን ተከናንቦ ተሰዷል፡፡ መለስ ዜናዊን እንመክራለን፤ልጃችን ነው ያዳምጠናል፤ ብልህ ነው ይገባዋል፤ ከሻዕቢያ ተጣልቶ ኢትዮጵያን ወዷል፤ ወዘተ ወዘተ ያሉ ደግሞ ብዙዎች ነበሩ/ናቸው፡፡ መልሰ ዜናዊ ግን፥ ወይ ፍንክች፥ ከፀረ ኢትዮጵያ ትልሜ ወይ ንቅንቅ ብሎ ባደቆነው የህገር ማፍረስ አባዜ እንደቀጠለ ነው፡፡ ተመክሮ ወይም በውዴታ የሚለወጥ ላለመሆኑ በምርጫው ዙሪያ የተካሄደውና እየተካሄደ ያለው ሌላ ምስክር ነው፡፡ መለስና ቡድኑ ሊመከሩ የሚችሉት ነቀንቆ በሚጥላቸውና በሚያሯሩጣቸው የሕዝብ አመፅ ብቻ ነው፡፡ ሌላ መንገድ የለም፡፡ በኖረና በደስታ በተቀበልነው ነበር፡፡ ግን የለም፡፡ አይኖርምም፡፡ ቅራኔው መሰረታዊና የማይታረቅ ነው፡፡ ወይ ሕዝብ ያሸንፋል ወይም የመለስ ቡድን አሸንፎ ይቀጥላል፡፡ ግብግቡ ደግሞ የእነ መለስ አሻናፊነት ከወዲሁ በተረጋገጠበት ምርጫ ተብዬ ዙሪያ አይደለም፡፡ የመለስን አገዛዝ ማሸነፍ ስንል ከሥልጣን አስወግዶ በሕዝባዊ መንግሥት፤ በዴሞክራሲያዊ መንግሥት መተካት ማለታችን ነው፡፡ መሠረታዊውን ቅራኔ በትግልና በድል መፍታት ማለታችን ነው፡፡ለዚህም ነው መለስተኛ ቅራኔዎችን በልክና በአግባብ ይዘን በህብረት ትግል አገዛዙ  ለማስወገድ እንታገል ሲል ኢሕአፓ ጥሪ የሚያደርገው፡፡